የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

በኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ

ከጥቅምት 19-26/2017ዓ.ም

(29 October –November 5/2024)

Week Four

## 1.የእንስሳት መኖ አቀነባባሪዎች በተጨማሪ እሴት ታክስ ምክንያት ከገበያ እየወጣን ነው አሉ

*ሪፖርተር፡ November 3, 2024*

በእንስሳት መኖ ላይ በተጣለው ተጨማሪ እሴት ታክስ ምክንያት ለኪሳራ መዳረጋቸውንና ሊዘጉ መቃረባቸውን፣ ሦስት የእንስሳት መኖ አቀነባባሪዎች አስታወቁ፡፡

የጉመራ የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ የንግድ መምርያ ኃላፊ አንድነት አሰፋ (ዶ/ር) የእንቁላል ጣይ ዶሮዎች መኖ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከመጣሉ በፊት በኩንታል 4,050 ብር ይሸጡ እንደነበር፣ አሁን ግን 4,820 ብር መድረሱን ተናግረዋል፡፡

በአንድ ኩንታል 700 ብር ጭማሪ በመደረጉ ከፋብሪካው መኖ ይገዙ የነበሩ ዶሮ አርቢዎች ከገበያ በመውጣታቸው፣ የመኖ ሽያጫቸው በሁለት ወራት ውስጥ 35 በመቶ ቅናሽ ማሳየቱን ገልጸዋል፡፡

ዶሮ አርቢዎች አዲሱን ዋጋ መቋቋም አቅቷቸው ከገበያ መውጣታቸውን፣ በዚህም ምክንያት ፋብሪካቸው መኖ ገዥ እንዳጣ ተናግረዋል፡፡

በየሠፈሩ ተጨማሪ እሴት ታክስ የማይከፍሉ መኖ አምራቾች በቅናሽ ስለሚያቀርቡ፣ የተቀሩት ዶሮ አርቢዎች ወደ እነሱ በመሄዳቸው ፋብሪካቸው ለኪሳራ መዳረጉን አንድነት (ዶ/ር) አክለዋል፡፡

ትልልቅ ፋብሪካዎች የእንቁላል ጣይ ዶሮዎች መኖ በኩንታል 4,820 ብር የሚሸጡ መሆኑን፣ ነገር ግን በማኅበር የተደራጁት ዋጋ በ4,000 እና በ3,900 ብር መካከል በመሆኑ፣ ደንበኞቻቸው ወደ ማኅበራቱ መሄዳቸውን ጠቁመዋል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/135031/

## 2.ለስታርትአፕ ብድር ብሔራዊ የዋስትና ማዕቀፍ የሚፈቅድ ረቂቅ ፖሊሲ ለግምገማ ቀረበ

**ሪፖርተር፡ October 30, 2024**

ለስታርትአፕ ብድር ከመስጠት ጋር የተያያዙ ሥጋቶችን ለመቀነስ የሚያስችል ብሔራዊ የብድር ዋስትና ማዕቀፍ እንዲዘጋጅ የሚያደርግ ረቂቅ ፖሊሲ ለግምገማ ቀረበ፡፡

በስታርትአፕ ኢትዮጵያ የሚኒስትሮች ኮሚቴ ቴክኒክ ቡድን የተዘጋጀው የስታርታአፕ ልማት የመጀመርያ ምዕራፍ ረቂቅ ፖሊሲ በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ የሚገኙ ስታርታፖችን ለማገዝ ከባለሀብቶች፣ ከመንግሥት ተቋማትና ከልማት ድርጅቶች የሚገኝ ካፒታል የሚያሰባስብ ፈንድ እንዲቋቋም ይጠይቃል፡፡

የሚቋቋመው ብሔራዊ የብድር ዋስትና አቅድ ሕጋዊ ሰውነት ያለው ገለልተኛ ተቋም ሆኖ የሚደራጅ ሲሆን፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ በሚዘጋጅ ደንብ መሠረት ቁጥጥር ይደረግበታል ተብሎ እንደሚጠበቅ በረቂቁ ተጠቅሷል፡፡

በተጨማሪም የብድር ዋስትና ማዕቀፉ ገለልተኛና ብቁ የዳይሬክተሮች ቦርድና ሥራ አስኪያጅ እንዲኖረው ተደርጎ ይቋቋማል፡፡ ቦርዱ ስትራቴጂካዊ ዕቅዶችን ሲያዘጋጅ፣ ሥራ አስኪያጅ ተደርጎ የሚሾመው ደግሞ የተቋሙን የዕለት ተዕለት ሥራ መምራትና የታለመለት ዕቅድ በአግባቡ እየተሳካ መሆኑን ማረጋገጥ ይጠበቅበታል ተብሏል፡፡

የግሉ ዘርፍ የነቃ ተሳትፎ እንዲያደርግ የሚያበረታታ ዘላቂ የፋይናንስ ሞዴል ከመቅረፅ ጀምሮ፣ ከመንግሥትና ከሌሎች ምንጮች የመቋቋሚያ ፋይናንስ (Seed Finance) እንደሚኖር ረቂቅ ፖሊሲው ያስረዳል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/135001/

## 3. በራሳቸው የውጭ ምንዛሪ ጥሬ ዕቃ ወደ አገር የሚያስገቡ ኩባንያዎች በኤሌክትሮኒክ ማጓጓዣ ሰነዶች እንዲገለገሉ ተፈቀደ

**ሪፖርተር፡ October 30, 2024**

የጉምሩክ ኮሚሽን በራሳቸው የውጭ ምንዛሪ (ፍራንኮ ቫሉታ) ጥሬ ዕቃ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቡ ኩባንያዎች የሚያቀርቧቸው የኤሌክትሮኒክ የማጓጓዣ ሰነዶች ተቀባይነት አግኝተው እንዲገለገሉ ፈቀደ፡፡

ሪፖርተር የተመለከተውና በጉምሩክ ኮሚሽነሩ አቶ ደበሌ ቃበታ ተፈርሞ ለሁሉም የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ለሚፈጸምባቸው ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች የተመራው ደብዳቤ እንደሚያስረዳው፣ ሌሎች በሕግ የተገለጹ ደጋፊ ሰነዶች መሟላታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በራሳቸው የውጭ ምንዛሪ (ፍራንኮ ቫሉታ) ሥርዓት ጥሬ ዕቃ ወደ አገር የሚያስገቡ ኩባንያዎች ብቻ የሚያቀርቡት የቴሌክስ ሪሊዝ (Telex Release)፣ ሲ ዌይቢል (Sea Waybill) ሰነዶች እንደ መጓጓዣ ሰነድ ተቀባይነት አግኝተው ተገቢው አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፡፡ ቴሌክስ ሪሊዝ (Telex Release) ግዥ ለተፈጸመበት ዕቃ መርከብ ላይ መጫኑ ሲረጋገጥ አጓጓዡ ወይም የአጓጓዡ ወኪል (Agent) በየትኛውም ቅርንጫፍ ዋናውን ቅጂ በማስገባት (Surrendered)፣ ሰነዶቹን የተቀበለው አጓጓዥ ድርጅትም ሆነ የአጓጓዡ ወኪል ዋናውን ቅጂ መቀበሉን በማረጋገጥ ለመዳረሻ ወደብ (Destination Port) ዕቃው እንዲለቀቅ በኤሌክትሮኒክ መልዕክት የሚያስተላልፍበት ሥርዓት ነው፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/134912/

## 4. ሀገራዊ ሪፎርም ከተጀመረ በኋላ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሬ የመጠባበቂያ ክምችት በእጥፍ አድጓል

**ኢዜአ፡ ጥቅምት 26/2017**

ሀገራዊ ሪፎርም ከተጀመረ በኋላ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሬ የመጠባበቂያ ክምችት በእጥፍ ማደጉን የብሔራዊ ባንክ ገዥ ማሞ ምሕረቱ አስታወቁ፡፡ አዲሱ የብሔራዊ ባንክ ማሻሻያ አዋጅ ከዚህ ቀደም ለረዥም ዓመታት ሲሠራበት የቆየውንና ለዋጋ ንረት ዋና መነሻ ነበር ሲባል በቆየው አሠራር ላይ ጠበቅ ያለ የማሻሻያ ድንጋጌ ይዞ መቅረቡን የብሔራዊ ባንክ ገዥ ማሞ ምሕረቱ ከሴንትራል ባንኪንግ መጽሔት ጋር ባደረጉት ቆይታ አስታውቀዋል፡፡ የብሔራዊ ባንክ ግብ የፋይናንስና የዋጋ ንረትን ማረጋጋት እንደሆነ በመጥቀስ አዲሱ ረቂቅ አዋጅና፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን የወጡ አዋጆችም ይህንኑ ግብ ለማሳካት በሚያስችል መንገድ ማሻሻያ እንደሚደረግባቸው ጠቅሰዋል፡፡ ይህን ተከትሎ ሀገራዊ ሪፎርሙ ከተጀመረ በኋላ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የውጭ ምንዛሬ የመጠባበቂያ ክምችት በእጥፍ ማደጉን ከመጽሔቱ ጋር በነበራቸው ቆይታ ተናግረዋል፡፡

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5402298

## 5. በአፍሪካ የመጀመሪያ የሆነው ኤርባስ ኤ350-1000 አውሮፕላን አዲስ አበባ ገባ

**ኢዜአ፡ ጥቅምት 26/2017**

የኢትዮጵያ አየር መንገድ ከኤር ባስ ኩባንያ የተረከበው የኤ 350-1000 አውሮፕላን ቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ ደርሷል። በቦሌ ዓለም አቀፍ አውሮፕላን ማረፊያ እየተካሄደ በሚገኘው አቀባበል የትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ሚኒስትር አለሙ ስሜ(ዶ/ር)፣ የቱሪዝም ሚኒስትር ሰላማዊት ካሳ እንዲሁም ሌሎች ከፍተኛ የመንግስት የስራ ሃላፊዎችን ጨምሮ ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ታድመዋል። የኢትዮጵያ አየር መንገድ በአፍሪካ የመጀመሪያ የሆነውን ኤ350-1000 "Ethiopia land of origins" የሚል ስያሜ የተሰጠውን የመንገደኞች አውሮፕላንን በትናንትናው ዕለት ከኤር ባስ የአውሮፕላን ኩባንያ መረከቡ ይታወቃል። በአፍሪካ የመጀመሪያ የሆነው የኤ 350-1000 አውሮፕላን ለአየር መንገዱ ቀጣይ ዕድገት ትልቅ ስኬት ስለመሆኑ ተጠቅሷል።

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5403719

## 6. የቁልፍ መሠረተ ልማቶችን የሳይበር ደህንነት ለመጠበቅ

**Ethiopian Press: November 5, 2024**

በዓለም አቀፍ ደረጃ የሳይበር ደህንነት ስጋት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መምጣቱን ተከትሎ የሳይበር ጥቃቶች እየተበራከቱ አሳሳቢ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ ይገኛሉ። ከሚሰነዘሩት የሳይበር ጥቃቶች ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት ደግሞ በቁልፍ መሠረተ ልማቶች ላይ የሚደረጉት መሆናቸውንም መረጃዎች ይጠቁማሉ።

መረጃዎቹ እንደሚያመላክቱት፤ በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ የተቃጡ ጥቃቶች ብዙ ችግሮችን ያስከትላሉ። ለአብነት እ.ኤ.አ.በ2021 በአሜሪካ የኮሎኒያል የነዳጅ ማስተላለፊያ መስመር ላይ የተፈፀመው የሳይበር ጥቃት ከፍተኛ የነዳጅ እጥረት ከማስከተሉ ባሻገር የሳይበር ጥቃት መሰረታዊ አገልግሎቶችን እንዴት ማስተጓጎል እንደሚችሉ ያሳየ ክስተት ሆኗል።

በኢትዮጵያም የሳይበር ጥቃት ሙከራው እየጨመረ መምጣቱን መረጃዎች ያመላክታሉ። ባለፈው ዓመት ከተከሰቱ 8ሺ854 የሳይበር ጥቃት ሙከራዎች መካከል ከፍተኛው ድርሻ የሚይዘው በቁልፍ መሰረተ ልማቶች ላይ የተሞከሩት ናቸው። ይህም አብዛኛዎቹ የሳይበር ጥቃቶች የሚያነጣጥሩት ቁልፍ መሠረተ ልማቶች ላይ መሆኑን ያሳያል።

https://press.et/?p=140068

# በውጭ ቋንቋዎችና ከውጭ ሚዲያዎች

## 7. ECX, Coffee Authority brews new pricing system following exchange rate float

**Reporter: November 2, 2024**

The Ethiopian Commodity Exchange (ECX) has introduced a new pricing mechanism for coffee sold on its trading floor but exporters say the changes do not reflect the high prices erasing their margins in the domestic market.

Officers at the Exchange and officials at the Ethiopian Coffee and Tea Authority say the new pricing system, which is updated weekly based on the New York Arabica Coffee Price and the prevailing exchange rate at the Commercial Bank of Ethiopia, is meant to benefit coffee growers.

A statement from ECX indicates distortions in the country's exchange rate policy had previously forced it to implement a comparative pricing mechanism accounting for domestic market a nd export prices. However, the recent liberalization of the forex market has enabled it to shift towards the new pricing system, according to the statement.

https://thereporterethiopia.com/42478/

## 8. Shipping Enterprise readies for massive fleet expansion plans

**Reporter: October 26, 2024**

Executives of the state-owned Ethiopian Shipping and Logistics Services Enterprise (ESLSE) are moving ahead with plans to acquire six bulk cargo ships.

Wondimu Daba, ESLSE deputy CEO for Corporate Services, told *The Reporter* that the company board is contemplating the terms of the acquisition.

"We are fully prepared to get the six ships. The board is examining whether we should get them as a time charter, voyage charter or purchase them outright. We will then follow the standard bidding process," said the Deputy.

The sole operational multimodal shipping company in the country, ESLSE's 2023/24 performance report indicates that it handled 45 percent share Ethiopia's total 8.25 tons of dry cargo imported via ports in Djibouti.

The Enterprise also reported that it handled the export of more than 13 tons of goods by sea.

This week, Alemu Sime, minister of Transport and Logistics, told state media that ESLSE's capacity is still lacking compared to the country's international trade needs.

https://thereporterethiopia.com/42386/

## 9. Ethiopia's Official Highlights ILRI's Role in Supporting Country's Agriculture Dev't in Research, Capacity-building

**ENA: November 5/2024**

The International Livestock Research Institute (ILRI) is proudly celebrating its 50th anniversary, reflecting on a half-century of impactful contributions to Ethiopia's livestock sector.

During the anniversary event, State Minister of Agriculture Fikru Regassa highlighted ILRI's vital role as a catalyst for transforming livestock-based livelihoods, enhancing food security, and promoting sustainable agriculture in the country.

He emphasized the substantial benefits Ethiopia has gained from ILRI's research and capacity-building initiatives, particularly in the fields of animal genetics, health, and nutrition.

Fikru noted that ILRI's research has led to the development of superior livestock breeds, especially in dairy and poultry. He also pointed out significant advancements in animal health, focusing on food safety and addressing challenges such as antimicrobial resistance and disease management.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5404503

## 10. Africans Urged to Expedite Implementation of AfCFTA as Crucial Instrument to Realize Integration

ENA; November 5/2024

Addis Ababa, November 5/2024 (ENA) Ethiopia's State Minister of Trade and Regional Integration, Yasmin Wohabrebbi has stressed the need for full implementation of the historic and transformative African Continental Free Trade Area (AfCFTA) agreement.

The 19th meeting of the committee of AfCFTA Senior Trade Officials (STOs) is taking place in Addis Ababa.

Opening the three-day meeting today, the state minister said African Continental Free Trade Area (AfCFTA) is a transformative agreement for trade integration in Africa.

Ethiopia has been undertaking notable economic reforms including the financial sector, telecom, and opening up of import and export trade, among others, the state minister pointed out.

As the reform promotes trade integration, Ethiopia is laying successful implementation mechanism of AfCFTA as well, it was indicated.

The state minister stressed the need for the full implementation of the AfCFTA which is crucial for realizing economic integration of the continent.

Chief technical advisor at AfCFTA Secretariat, Tsotetsi Makong said AfCFTA is instrumental to transform trade landscape in Africa and realize a unified market in the continent.

This continental agreement is a game changer in Africa's inclusive development and pivotal for fulfilling the goal of realizing one Africa market.

It is not only a trade agreement, he said, adding it is a shared prosperity in Africa.

Similarly, Chairperson of the STOs Hashil Abdalah affirmed that AfCFTA is an important pillar for the economic social and political development of the continent.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5402007